https://www.path-2-happiness.com/am

الطريق إلى السعادة
The Path to Happiness

https://www.path-2-happiness.com/am

የመልካም ስነምግባር መንገድ

ማውጫ

የመልካም ስነምግባር መንገድ

እምነት፡ ከመልካም ስነ ምግባር ጋር የተሳሰረ መሆኑ፡፡

ፅባዳዎችና ስነምግባር፡

ስነምግባር እስላም ውስጥ

https://www.path-2-happiness.com/am

የመልካም ስነምግባር መንገድ

የደስተኝነትና የመታደል መንገድ፣ ግብረ ገብነትና መልካም ስነምግባር የሚውለበለብበት መንገድ መሆኑ የግድ ነው። በዚህ መንገድ የሚጓዝ መንገደኛም መንገዱን በፍቅር፣ በመቻቻል፣ በቸርነት፣ በይቅርታ፣ በይሉኝታ፣ በሰላም፣ በትህትና፣ በመተሳሰብ፣ በፍትሕ፣ በሐቀኝነት፣ በምክክርና በተቀሩትም መልካም ስነምግባራት የተሞላ ሆኖ ማግኘቱም የግድ ነው። በተጨማሪም ከነፍሲያና ከፍላጎቶቿ በላይ በመሆን ወደ ከፍተኛው የሞራል ደረጃና ወደ ምሉእ ስነምግባር የሚመጠቅበት መንገድም ነው። መልካም ስነምግባር ሊያስቀሩት የሚቻል የቅንጦት እቃ ሳይሆን በሕይወት ውስጥ ወሳኝነት ካላቸው መሰረቶች ቀዳሚውን ቦታ የሚይዝ ነው። የግለሰቦች መልካም ጠባይና ጥሩ ግብረገብነት፣ በራሳቸውና በሕብረተሰቦቻቸው የደስተኝነት ሕይወት ላይ ገንቢ ነፀብራቅ ይኖረዋል። መጥፎና ብልሹ ከሆነ ደግሞ የሁሉም ሕይወት ብልሹና ደስተኝነት የራቀው ይሆናል።

ለዚህ ነው እስላም በተከታዮቹ ዘንድ የመልካም ስነምግባር ቡቃያን ለመዝራት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠውና እንዲላበሱት አጥብቆ የሚያሳስባቸው። የአላህ መልክተኛ ﷺ የተላኩበት ዓላማ መልካም ስነምግባራትን የተሟሉ ማድረግ መሆኑን ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹የተላክሁት መልካም ስነምግባራትን ምሉእ ለማድረግ ነው።›› [በበይሀቂ የተዘገበ] የሰው ልጅ ካወቃቸው ስልጣኔዎች ታላቁን ስልጣኔ በመገንባት ዘመናትን የተሻገረውና የመልክቱ ባለቤት ብርሃኑን ለማዳረስና ሰዎችን በዙሪያው ለማሰባሰብ ከፍተኛ ትግል ያደረጉበት የእስላም መልክት፣ አቢይ ዓላማው የሰው ልጆችን ባሕሪ ማረቅ፣ ስነምግባራቸውን ማነጽና የምሉእነት አድማስን ከፊታቸው ወለል አድርጎ መክፈት ነበር ማለት ይቻላል።

የነቢዩ ﷺ መላክም መልካም ስነ ምግባርን ለማጎልበት፣ ነፍስን ለማጥራትና ለማነጽ ነበር። እሳቸው ሲላኩ ሰዎች ከነዚህ መልካም ስነ ምግባራት ብዙዎቹን የሳቱ፣ ከፊሎቹን የማያውቋቸውና ምንም ግምት የማይሰጧቸው ነበሩ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ ٱلَّذِي بَعَثَ فِي ٱلۡأُمِّيِّـۧنَ رَسُولٗا مِّنۡهُمۡ يَتۡلُواْ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتِهِۦ وَيُزَكِّيهِمۡ وَيُعَلِّمُهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَإِن كَانُواْ مِن قَبۡلُ لَفِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٖ ۝٢}[الجمعة: ٢]،

‹‹እርሱ ያ በመሃይሞች ውስጥ አንቀጾቹን (ቁርአንን)፣ በነርሱ ላይ የሚያነብላቸው፣ (ከማጋራት) የሚያጠራቸውም፣ መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸው የኾነን መልክተኛ (መሐመድን) ከነሱው ውስጥ የላከ ነው፤ እነርሱም ከርሱ በፊት በግልጽ ስሕተት ውስጥ ነበሩ።››[አልጁሙዓ፡2]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{كَمَآ أَرۡسَلۡنَا فِيكُمۡ رَسُولٗا مِّنكُمۡ يَتۡلُواْ عَلَيۡكُمۡ ءَايَٰتِنَا وَيُزَكِّيكُمۡ وَيُعَلِّمُكُمُ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَيُعَلِّمُكُم مَّا لَمۡ تَكُونُواْ تَعۡلَمُونَ ۝١٥١} [البقرة: ١٥١]

‹‹በውስጣችሁ ከናንተው የኾነን በናንተ ላይ አንቀጾቻችንን የሚያነብላችሁና

የስነምግባር መሰረቶች

‹‹የስነምግባር መሰረቶች ቁርአን ውስጥ ከፍ ያሉ ናቸው፤ በርሱ ያመኑ ሕዝቦች ለዒሳ ሃይማኖት ያደሩ ሕዝቦች እንደተለወጡ ሁሉ በዘመን ለውጥ ተለውጠዋል። ከዚህ ጨምቆ ማውጣት የሚቻለው ዋነኛው ውጤት ለሕግጋቱ ባደሩ ሕዝቦች ላይ ቁርአን ያሳደረው ታላቁ ቁርአን ያሳደረው ተጽእኖ ነው። እስላም በሰዎች ልቦና ላይ ያለውን ሥልጣን ሃይማኖቶች በጣም ጥቂት ናቸው። ለእስላም ያጋጣመውን ቋሚ ተጽእኖ የማሳደር ብቃት ያጋጠመው ሌላ ሃይማኖት ላይኖር ይችላል። ቁርአን በምስራቁ ዓለም የሕይወት ዋልታ ነው፤ ዱካው በጥቃቅኑ ዝርዝር የአነዋነዋር ጉዳዮች ውስጥ የሚስተዋል ነው።››

ጉስታፍ ሊቦን

ፈረንሳዊ ታሪክ ጸሐፊ

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

የሚያጠራችሁ፣መጽሐፍንና ጥበብንም የሚያስተምራችሁ፣ታውቁት ያልነበራችሁትንም ነገር የሚያሳውቃችሁ የኾነን መልክተኛ እንደላክን (ጸጋን ሞላንላችሁ)።››[አልበቀራህ፡151]እምነት ከመልካም ስነ ምግባር ጋር የተሳሰረ መሆኑ፦

ኢማን አማኙን ወደ በጎ ነገሮች የሚገፋፋና ክፉና ውጉዝ ነገሮችም የሚከለክለው ኃይል ነው። መልካም ስነምግባር የጠንካራ ኢማን ምልክት እንደሆነ ሁሉ፣የመልካም ስነ ምግባር መላሸቅም የኢማን ድክመት ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል። የአላህ መልክተኛ ﷺ ጠንካራ ኢማን የግድ ጠንካራ መልካም ስነምግባርን እንደሚወልድ፣የመልካም ስነምግባር መዝቀጥ መንስኤም የኢማን መዳከም ወይም ጨርሶ አለመኖር መሆኑን አብራርተዋል። አማኝ ያልሆነ ሰው ምንም ግድ ሳይኖረው፣ይሉኝታና ወቀሳን ሳይፈራ፣በሚፈጽመው ኃጢአት እጠየቅበታለሁ ብሎ ሳይጨነቅ ወራዳ ተግባራትን ይፈጽማል። የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ይሉኝታና ኢማን አንድ ላይ የተቆራኙ ናቸው፤አንደኛው ሲወገድ ሌላኛውም ይታጣል።›› [በበይሀቂ የተዘገበ] ከጎረቤት ጋር በሚኖረው ግንኙነት ኢስነምግባራዊ መሆን ኢማንን የሚጻረር መሆኑን ሲያመለክቱም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹በአላህ እምላለሁ፣አያምንም፤በአላህ እምላለሁ፣አያምንም፤በአላህ እምላለሁ፣አያምንም፤›› ሲሉ የአላህ መልክተኛ ሆይ! ምንድነው እርሱ? አሏቸው። ‹‹ጎረቤቱ ከርሱ ክፋት የመዳን መተማመኛ የሌለው ሰው ነው።›› [በቡኻሪ የተዘገበ]

ከዚህም ስንነሳ፣አላህ (ሱ.ወ.) ባሮቹን ወደ በጎ ነገር ሲጠራ ወይም ከክፉ ነገር ሲያስጠነቅቃቸው ይህን የሚያደርገው በልቦቻቸው ውስጥ በጸናው ኢማን መሰረት መሆኑን እንገነዘባለን። አላህ (ሱ.ወ.) መጽሐፉ ውስጥ ብዙ ጊዜ እንዲህ ይላል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ} ‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ!››

ከዚህ ዓይነቱ ሐረግ በማስከተልም የሚፈለግባቸውን ያወሳል። የሚከተለውን የመሳሰለ ማለት ነው፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَكُونُواْ مَعَ ٱلصَّٰدِقِينَ ١١٩} [التوبة: ١١٩]،

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፤ከውነተኞችም ጋር ኹኑ።››[አልተውባህ፡119]

እንደዚሁም የአላህ መልክተኛ ﷺ ተከታዮቻቸውን ስለ መልካም ስነምግባር ሲያስተምሩ ከእምነት ጋር እያያዙ ያስተምሩ ነበር። ለአብነት የሚከተለውን የነቢዩን ﷺ ቃል እናገኛለን፦ ‹‹በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው፣እንግዳውን ያስተናግድ፤በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው፣የጎረቤቱን መብት ይጠብቅ፤በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው፣መልካም መልካሙን ይናገር ወይም ዝም ይበል። [በአሕመድ የተዘገበ] ምግባረ ሰናይነትን ነፍስ ውስጥ ለማነጽ በዚህ መልኩ ነው እስላም በእምነት እውነተኛነትና በምሉእነቱ ላይ የሚመረኮዘው።

https://www.path-2-happiness.com/am

ዕባዳዎችና ስነምግባር፦

ዕባዳ ወይም አምልኮተ አላህ እስላም ውስጥ እንዳው ስውር ቃላትና ትርጉም የለሽ እንቅስቃሴዎች ሳይሆን፣መንፈስን የሚያጠሩና ሕይወትን አስደሳች የሚያደርጉ ተግባራትና ቃላት መገለጫ ነው። እስላም ውስጥ የሃይማኖታዊ ግዴታዎች ግብ፣ሁኔታዎች የፈለጉትን ያህል ቢለዋወጡ እንኳ ሙስሊሙ ሁሌም ምስጉን ምግባራትን ተላብሶና በመልካም ባሕርያት ጸንቶ እንዲኖር ማድረግ ነው። ቅዱስ ቁርኣንና የጸዳው ነቢያዊ ሱንና ይህንኑ እውነታ ያረጋግጣሉ። አላህ (ሱ.ወ.) የሶላት ግዴታን ሲደነግግ ሶላት ከመጥፎ ስነምግባርና ከሚጠላ ነገር የሚከለክል መሆኑን በማለጽ እንዲህ ብሏል፦

{ٱتْلُ مَآ أُوحِيَ إِلَيْكَ مِنَ ٱلْكِتَٰبِ وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَۖ إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ تَنْهَىٰ عَنِ ٱلْفَحْشَآءِ وَٱلْمُنكَرِۗ وَلَذِكْرُ ٱللَّهِ أَكْبَرُۗ وَٱللَّهُ يَعْلَمُ مَا تَصْنَعُونَ ٤٥} [العنكبوت: ٤٥].

‹‹ከመጽሐፉ ወደ አንተ የተወረደውን አንብብ፤ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፤ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፤አላህንም ማውሳት ከሁሉ ነገር በላጭ ነው፤አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃል።››[አልዐንከቡት፡45]

ዘካም እንደዚሁ እስላም ውስጥ፣የእዝነትና የመተሳሰብን ቡቃያ የሚዘራ፣የትውውቅ የትብብርና የቅርርብ ግንኙነቶችን በሕብረተሰቡ የተለያዩ መደቦች መካከል የሚፈጥርና የሚያጠናክር የላቀ ግብ ያለው ዕባዳ እንጂ እንዳው ለድሆች ሊሰጥ ከሀብታሞች የሚወሰድ ተራ ግብር ብቻ አይደለም። የከፋዩን ነፍስ ከንፍገት ቆሻሻ ማጥራትና ሕብረተሰቡን ወደ ላቀ በይነሰባዊ ግንኙነት ደረጃ ከፍ ማድረግ የዘካ ቀዳሚ ጥበብ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

መጥፎ ልማዶች

ቶሊስቶይ
ሩሲያዊ የስነጽሑፍ ሰው

https://www.path-2-happiness.com/am

{خُذۡ مِنۡ أَمۡوَٰلِهِمۡ صَدَقَةٗ تُطَهِّرُهُمۡ وَتُزَكِّيهِم بِهَا وَصَلِّ عَلَيۡهِمۡۖ إِنَّ صَلَوٰتَكَ سَكَنٞ لَّهُمۡۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ١٠٣} [التوبة: ١٠٣]؛

‹‹ከገንዘቦቻቸው ስትሽን በርሷ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የሽነትን ምጽዋት ያዝ፤ ለነሱም ጸልይላቸው፤ ጸሎትህ ለነርሱ እርካታ ነውና፤ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው።››[አልተውባህ፡103]

በመሆኑም ምጽዋት (ሶደቃ) ገንዘብ በመለገስ ብቻ ላይ የተወሰነ አልተደረገም። ሕብረተሰቡንና ግለሰቦችን ደስተኞች ለማድረግ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ በርካታ መልካም ስነምግባሮችንም እንዲያካትት ተደርጓል። ነቢዩ ﷺ አንድ ሙስሊም መለገስ ያለበትን ሶደቃ ትርጓሜ ሰፋ አድርገው ሲያቀርቡ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ከራስህ ባልዲ ወደ ወንድምህ ባልዲ ውሃ መገልበጥህ ሶደቃ ነው፤ በበጎ ነገር ማዘዝህና ክክፎ ነገር መከልከልህም ሶደቃ ነው።›› በሌላ ዘገባ ደግሞ ‹‹በወንድምህ ፊት ፈገግ ማለትህም ሶደቃ ነው፤ ሰዎች ከሚሄዱበት መንገድ ላይ ድንጋይ፤ እሾህና አጥንት ማስወገድህም ሶደቃ ነው፤ በአሳሳች ቦታ ወንድምህን (መንገድ) መምራትህም ሶደቃ ነው›› የሚል ተመልክቷል። [በበይሀቂ የተዘገበ]

እስላም ጾምንም እንደዚሁ ከምግብና ከመጠጥ መከልከል ብቻ አድርጎ አይመለከትም። የድሆችንና የአጦችን ስሜት ለመረዳት የሚያግዝ፤ በተመሳሳይም ነፍስን ለማሰልጠንና ፍላጎቶቿንና ዝንባሌዎቿን ለመቆጣጠር የሚያስችል የመልመጃና የስልጠና ትምህርት ቤት አድርጎ ነው የሚመለከተው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ١٨٣} [البقرة: ١٨٣]،

‹‹እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ)፤ ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።››[አልበቀራህ፡183]

የአላህ መልክተኛም ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹በሐሰት መመስከርን እና በዚያ መሰረት መስራትን እርግፍ አድርጎ ያልተወን ሰው፤ ምግብና መጠጡን ከመተው አላህ ጉዳይ የለውም።›› [በአሕመድ የተዘገበ] በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ጾም ምግብና መጠጥን መተው (ብቻ) አይደለም፤ ከውዳቂ ዝባዝንኬና ከብልግና ቃል መጾም ነው እንጅ፤ አንድ ሰው ቢሰድብህ ወይም ቢጣላህ፦ እኔ ጾመኛ ነኝ፤ እኔ ጾመኛ ነኝ በልም።›› [በኢብን ኹዘይማ የተዘገበ]

ሐጅን በተመለከተም ሌሎች ሃይማኖቶች አንዳንዴ የማይታወቁ ሚስጥራዊ አምልኮዎችን የሚያካትቱ ከመሆናቸው አንጻር፤ አንድ ሰው ስነምግባራዊ ይዘቶች የሌሉት ባዶ ጉብኝት አድርጎ ሊገምት ይችል ይሆናል። ይህ ፈጽሞ ስህተት ነው። ይህን ሥርዓተ ጸሎት አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلۡحَجُّ أَشۡهُرٞ مَّعۡلُومَٰتٞۚ فَمَن فَرَضَ فِيهِنَّ ٱلۡحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِي ٱلۡحَجِّۗ وَمَا تَفۡعَلُواْ مِنۡ خَيۡرٖ يَعۡلَمۡهُ ٱللَّهُۗ وَتَزَوَّدُواْ فَإِنَّ خَيۡرَ ٱلزَّادِ ٱلتَّقۡوَىٰۚ وَٱتَّقُونِ يَٰٓأُوْلِي ٱلۡأَلۡبَٰبِ ١٩٧} [البقرة: ١٩٧]

‹‹ሐጅ (ጊዜያቱ) የታወቁ ወሮች ናቸው፤ በነርሱም ውስጥ ሐጅን (እንዲሠራ) ነፍሱን ያስገደደ ሰው፤ በሐጅ ውስጥ ሴትን መገናኘት፤ ማመጥም፤ ክርክርም፤ የለም፤ ከበጎም ሥራ የምትሠሩትን ሁሉ አላህ ያውቀዋል፤ ተሰነቁም፤ ከስንቅም ሁሉ በላጩ ጥንቃቄ ነው፤ የአእምሮዎችም ባለቤቶች ሆይ! ፍሩኝ።››[አልበቀራህ፡197]

ከላይ የቀረቡት ሁሉ በሃይማኖትና በመልካም ስነምግባር መካከል ያለው ትስስር በጣም የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣሉ። እስላም ውስጥ ሶላትን፤ ጾምን፤ ዘካንና ሐጅን የመሳሰሉ ዋነኞቹ የእስላም ማእዘናት፤ የተቀሩት ሌሎች የመግዛት ሥራዎችም፤ በምስጉን ስነምግባርና በመጠቁ መርሆዎች ጥላ ስር፤ የሰውን ልጅ ወደሚያልመውና በደስተኝነትና በመረጋጋት ወደታደለው ምሉእነት ሕይወት የሚወስዱ መንገዶች ናቸው። ዕባዳዎቹ በአፈጻጸማቸውና በቅርጻቸው የተለያዩ ቢሆኑም፤ የአላህ መልክተኛ ﷺ ‹‹የተላክሁት መልካም ስነምግባራትን ምሉእ ለማድረግ ነው›› በማለት ባስቀመጡት አንድ ግብ ላይ ሁሉም ይገናኛሉ። ስለዚህም የደስተኝነትና የመታደል መንገድ በስነምግባር ላይ የሚመረኮዝና በዚህ ምሕዋር ዙሪያ የሚሽከረከር፤ ምስጉን ባሕርያትና ዕባዳ ፈጽሞ የማይነጣጠሉበት መንገድ ነው።

ሕግና ሞራል

‹‹በእስላም እምነት ውስጥ በሕጋዊ አስገዳጅነትና በሞራላዊ አስገዳጅነት መካከል ልዩነት የለም። በሕግና በሞራላዊ ስነምግባር መካከል ያለው ይህ ጥብቅ ሕብረት ከጅማሮው የሥርዓቱን ጥንካሬ ያረጋግጣል።››

ማርሴል በዋሃር

ፈረንሳዊ አሳቢ

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

የጥቃቅን ዝርዝር ጉዳዮች መሰረቶች

‹‹ቁርኣን ለሁሉም ጉዳዮች መፍትሔዎችን ያቀርባል። ሃይማኖታዊውን ሕግ ከሞራላዊው ሕግ ጋር ያስተሳስራል። ማሕበራዊ ሥርዓትና አንድነትን ለመፍጠር፣ ተስፋ የለሽነትን ጭካኔንና አፈተረትን ለማቃለል ጥረት ያደርጋል። የጎስቋሎችን እጅ ለመያዝ ጥረት በማድረግ ደግነትን ይመክራል፤ በመተዛዘንና በርህራሄ ያዛል። በሕግ አወጣጥ ረገድ ለዕለታዊ ተራድኦ ለጥቃቅን ዝርዝር ጉዳዮች መሰረቶችን ያኖራል። ለውሎችና ለውርስ ጉዳዮች ሥርዓት አብጅቶላቸዋል። በቤተሰብ መስክ እያንዳንዱ ግለሰብ በሕጻናት፣ በአገልጋዮችና በእንስሳት አያያዝ፣ በጤናና በአባበስ ጉዳዮች ላይ መከተል ያለበት ወሰኖ አስቀምጧል . . ወዘተ. ››

ሻክ ሲ.. ረስለር
ፈረንሳዊ ተመራማሪ

ስነምግባር እስላም ውስጥ

የደስተኝነትና የመታደል መንገድ ሕጋዊ፣ እነጻዊና ዐቂዳዊ መሰረቶቹ በሁሉም ነገር ውስጥ የሚቆሙት በስነምግባር መደላድል ላይ ነው። ከአላህ (ሱ.ወ.) ጋር የሚኖረውን ግንኙት ከሚመለከተው አደብና ስነምግባር አንስቶ ከራስ ጋር፣ ከባልደረቦች ጋር፣ ከዘመዶች ጋር፣ ከጎረቤት ጋር፣ ሌላው ቀርቶ ከሚዋጋህ ጠላትም ጋር፣ ከእንስሳትና ከሁሉም ፍጥረታት ጋር፣ ከዚህም አልፎ ከተፈጥሮ አካባቢ፣ ከዛፎችና ከእጸዋትም ጋር . . በሁሉም ነገሮች ውስጥ መሰረቶቹ የሚቆሙት በስነምግባር መደላድል ላይ ነው። ይህ ሁሉ አንደበታዊ ስነምግባርን፣ አካላዊና ተግባራዊ ስነምግባርንና ሕሊናዊና ውስጣዊ ልቦናንም የሚያጠቃልል ነው። አላህ (ሱ.ወ.) አንደበታዊ ከሆኑ የመልካም ስነምግባር መርሆዎች አንዱን ሲያረጋግጥ እንዲህ ብሏል፦

{وَقُولُواْ لِلنَّاسِ حُسۡنٗا} [البقرة: ٨٣]،

‹‹ለሰዎችም መልካምን ተናገሩ፤ ››[አልበቀራህ:83]

ተግባራዊ የስነምግባር መርህን ሲያስቀምጥም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱدۡفَعۡ بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ ٱلسَّيِّئَةَۚ نَحۡنُ أَعۡلَمُ بِمَا يَصِفُونَ ٩٦} [المؤمنون: ٩٦]،

‹‹በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው (ጠባይ) መጥፎይቱን ነገር ገፍትር፤ እኛ የሚሉትን ሁሉ ዐዋቂዎች ነን።››[አልሙእሚኑን:96]

የአላህን መጽሐፍ አስተውሎ የተመለከተ ሰው፣ በስነምግባራዊ ትእዛዛት የተሞላ መሆኑን ይረዳል። ቀጥሎ የሰፈሩትን ቁርኣናዊ አንቀጾች እናስተውል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{هَلۡ جَزَآءُ ٱلۡإِحۡسَٰنِ إِلَّا ٱلۡإِحۡسَٰنُ ٦٠} [الرحمن: ٦٠]،

‹‹የበጎ ሥራ ዋጋ በጎ እንጅ ሌላ ነውን?››[አልረሕማን:60]

በተጨማሪም (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تَنسَوُاْ ٱلۡفَضۡلَ بَيۡنَكُمۡ} [البقرة: ٢٣٧]،

‹‹በመካከላችሁም ችሮታን አትርሱ፤ ››[አልበቀራህ:237]

በተጨማሪም (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَصَبۡرٞ جَمِيلٞۖ وَٱللَّهُ ٱلۡمُسۡتَعَانُ عَلَىٰ مَا تَصِفُونَ ١٨} [يوسف: ١٨]،

‹‹ስለዚህ መልካም ትእግስት (ማድረግ አለብኝ) በምትሉትም ነገር ላይ መታገዣው አላህ ብቻ ነው።››[ዩሱፍ:18]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِنَّ ٱلسَّاعَةَ لَأٓتِيَةٞۖ فَٱصۡفَحِ ٱلصَّفۡحَ ٱلۡجَمِيلَ ٨٥} [الحجر: ٨٥]،

‹‹ሰዓቲቱም በርግጥ መጪ ናት፤ መልካምንም ይቅርታ አድርግላቸው።››[አልሒጅር:85]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{خُذِ ٱلۡعَفۡوَ وَأۡمُرۡ بِٱلۡعُرۡفِ وَأَعۡرِضۡ عَنِ ٱلۡجَٰهِلِينَ ١٩٩} [الأعراف: ١٩٩]،

‹‹ገርን ጠባይ ያዝ፤ በመልካምም እዘዝ፤ ባለጌዎቹንም ተዋቸው።››[አልአዕራፍ: 199]

ፈጠራ ወሬና ማጠልሸት

ቶማስ ካርሊል

እስኮትላንዳዊ ሐያሲና ታሪክ ጸሐፊ

‹‹ጭፍንና ጠባብ ወገንተኞች፣ ሙሐመድ ከግለሰባዊ እውቅና ፍለጋ፣ ከገዢና እና ከሥልጣን ውጭ ሌላ ፍላጎት አልነበረውም ይላሉ። ፈጽሞ አይደለም፤ በእግዚአብሔር ይሁንብኝ በዚያ የታላቅ ሰብእና ባለቤት በሆነው፣ በእገዢነት፣ በሰናይነት፣ በአዘኔታ፣ በደግነትና በጥበብ በተሞላው በዚያ የምድረበዳ በረሃ ታላቅ ሰው ልብ ውስጥ ከዓለማዊ ሕይወት ስግብግብ ፍላጎት ውጭ የሆኑ ሀሳቦች፣ ከሥልጣንና ዝና ፍለጋ የራቁ ቅን ፍላጎትና ዓላማዎች ነበሩ። እንዴታ! ያ የጠራች ነፍስ ባለቤት የሆነ ከነዚያ ቅኖች፣ ፍጹሞችና የምሮች ከመሆን ውጭ ሌላ ምንም መሆን ከማይችሉ ሰዎች አንዱ ነውና!››

ፍትሐዊነትና ንጽሕና

‹‹ይህ ሰው ለእምነቶቹ ብሎ ግፍና ጭቆናን መቻሉ፣ መሪና አዛቸው አድርገውት ያመኑበትና ተከተሉት ሰዎች ያላቸው የመጠቀ ስነምግባርና ባሕሪ፣ ፍጹማዊ ከሆኑ ታላላቅ ስኬቶቹ ተደምሮ . . ይህ ሁሉ በሰብእናው ውስጥ የሰረጸውን ፍትሐዊነትና ንጽሕና ያመለክታል። ሙሐመድ አስመሳይ ነው የሚለው ግምት ችግሮችን ይበልጥ የሚያወሳስብ እንጂ የሚፈታ ግምት አይደለም። እንዲያውም ከምዕራባውያን ታላላቅ ታሪካዊ ሰብእናዎች ውስጥ ሙሐመድ ያገኘውን ተገቢ ክበሬታ ያገኘ አንድም ሰብእና የለም።››

ሞንትጎመሪ ዋት

እንግሊዛዊ ኦሪየንታሊስት

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذَا سَمِعُواْ ٱللَّغۡوَ أَعۡرَضُواْ عَنۡهُ وَقَالُواْ لَنَآ أَعۡمَٰلُنَا وَلَكُمۡ أَعۡمَٰلُكُمۡ سَلَٰمٌ عَلَيۡكُمۡ لَا نَبۡتَغِي ٱلۡجَٰهِلِينَ ٥٥} [القصص: ٥٥]፣

‹‹ውድቅንም ቃል በሰሙ ጊዜ፣ ከርሱ ይርቃሉ፤ ለኛ ሥራዎቻችን አሉን፤ ለናንተም ሥራዎቻችሁ አሏችሁ፤ ሰላም በናንተ ላይ (ይኹን)፤ ባለጌዎችን አንፈልግም ይላሉ፤ ››[አልቀሶስ፡55]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تَسۡتَوِي ٱلۡحَسَنَةُ وَلَا ٱلسَّيِّئَةُۚ ٱدۡفَعۡ بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ فَإِذَا ٱلَّذِي بَيۡنَكَ وَبَيۡنَهُۥ عَدَٰوَةٞ كَأَنَّهُۥ وَلِيٌّ حَمِيمٞ ٣٤} [فصلت: ٣٤].

‹‹መልካሚቱና ክፉይቱም (ጠባይ) አይተካከሉም፤ በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ጠባይ (መጥፎይቱን) ገፍትር፤ ያን ጊዜ ያ ባንተና በርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው፣ እርሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይኾናል።››[ሓ ሚም አልሰጅዳህ፡34]

የአላህ መልክተኛ ﷺ ስነምግባርም ቁርኣናዊ ስነምግባር ነበር። አላህ (ሱ.ወ.) ታላቅ ስነምግባራቸውን ሲያሞግስ እንዲህ ብሏል፦

{وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٖ ٤} [القلم: ٤]፤

‹‹አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ።››[አልቀለም፡ 4]

ለዚህም ነው ነቢዩ ﷺ፣ ከሌላው ነገር በተለየ ለመልካም ስነምግባር ልዩ ትኩረትና ትልቅ ደረጃ የሰጠ መልእክት ይዘው የመጡት። የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ከምእመናን መካከል ከሁሉም ይበልጥ ኢማኑ ሙሉ የሆነው ከሁሉም ይበልጥ መልካም ስነምግባር ያለው ነው፤ ምርጥና በላጫቸውም ለሴቶቻቸው ከሌሎቹ ይበልጥ ጥሩዎቹ ናቸው።›› [በቡይሀቂ የተዘገበ] በተጨማሪም የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹በጎ ነገር መልካም ስነምግባር ነው፤ ኃጢአት ልብህን የከነከነና ሰዎች እንዳያውቁት ብለህ የምጠላው ነገር ነው።›› [በሙስሊም የተዘገበ] እንደዚሁም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ብልግና እና መባለግ በእስላም ውስጥ ቦታ የላቸውም፤ ከሰዎች ሁሉ እስልምናው ይበልጥ ያማረው ከሁሉም ይበልጥ መልካም ስነምግባር ያለው ነው።›› [በአሕመድ የተዘገበ] በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹በትንሣኤው ቀን በአንድ አማኝ (የሥራዎች) ሚዛን ከመልካም ስነምግባር ይበልጥ ክብደት ያለው ምንም ነገር የለም፤ አላህ (ሱ.ወ.) ክፉ ባለጌን በእርግጥ ይጠላል።› [በቡይሀቂ የተዘገበ]

የአላህ መልክተኛም ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹በአኽራ ከሁሉም ይበልጥ ለኔ ተወዳጆቻችሁና ለኔ ከሁሉም ይበልጥ ቅርቦቻችሁ ከሁሉም ይበልጥ መልካም ስነምግባር ያላቸው ናቸው። ከሁላችሁም ይበልጥ እኔ ዘንድ የተጠሉትና ከሁሉም ይበልጥ ከኔ ሩቅ የሆኑት ደግሞ መጥፎ ስነምግባር ያላቸው፣ ነገር ከልክ በላይ መናገርን የሚያበዙ (ለፍላፊዎች)፣ ቀባጣሪዎችና ሲንጣጡ የሚውሉ ሰዎች ናቸው።›› [በአሕመድ የተዘገበ]

መልካም ስነምግባራት እስላም ውስጥ አጠቃላይና ምሉእ ሲሆኑ ቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው ነው፦

ከአላህ ጋር የሚኖር ግንኙነትን የሚመለከት መልካም ስነምግባር፦

ከአላህ (ሱ.ወ.) ጋር የሚኖረው አደብና መልካም ስነምግባር ሦስት ነገሮችን ያጠቃልላል፦

አንደኛ፦ በርሱ ማመንና ከርሱ ዘንድ የመጣውን ሁሉ ማረጋገጥ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) ስለራሱ እንዲህ ብሏል፦

{ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ لَيَجۡمَعَنَّكُمۡ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ لَا رَيۡبَ فِيهِۦۗ وَمَنۡ أَصۡدَقُ مِنَ ٱللَّهِ حَدِيثٗا ٨٧} [النساء: ٨٧]፣

‹‹አላህ ከርሱ በስተቀር አምላክ የለም፤ ወደ ትንሣኤ ቀን በርሱ ጥርጥር የሌለበት ሲኾን፣ በእርግጥ ይሰበስባችኋል። በንግግርም ከአላህ ይበልጥ እውነተኛ ማነው?››[አልኒሳእ፡87]

ከአላህ (ሱ.ወ.) የተላለፈ ቃሉን ማረጋገጥ፣ አንድ ሰው በአላህና በነቢዩ ﷺ ንግግር ምንም ጥርጣሬና ውዥንብር ሳይገባበት የሚያምንበት፣ የሚከላከልለት፣ በርሱም መንገድ የሚታገልለት መሆንን ግዴታ ያደርጋል።

ሉዊስ ሲዲዮ

ፈረንሳዊ ኦሪየንታሊስት

ፊሊጶሐዘር ለኽጫሩታ፦

‹‹የአላህን ፍቅር በጽኑ የሚገልጽ ቢሆን እንጂ አንድም አንቀጽ አታገኝም። ሞራላዊ ስነምግባርን በሚመለከቱ መሰረቶች አማካይነት ለትሩፋት ሥራ ከፍተኛ የሆነ ማበረታቻ ይሏል። ለመዋደድና ለመተሳሰብ፣ ለቅን ልቦና እና ቀየሜታን በይቅርታ ስለማለፍ ታላቅ ጥሪ አካቷል። ለኩራት፣ ለጉራና ለቁጣ ጥላቻን ይሏል። ኃጢአት በማሰብና በማየትም ሊፈጠር እንደሚችል የሚያመለክት ነገርም አለበት። ከካፊሮች ጋር ቢሆን እንኳ ቃል ኪዳንን ማክበርን፣ ትህትናንና ትእቢተኛ አለመሆንን የሚያበረታታ ነገርም አጣሏል። በቁርኣን ውስጥ ያለውን የመልካም ስነምግባር መሰረቶች ጥራት ለማረጋገጥ፣ እነዚያ በጥበብና በቅን መመሪያ የተሞሉ የአጠቃላይ አነጋገር ስብስቦች ብቻ በቂ ናቸው። ቁርኣን ሁሉንም ነገሮች ተመልክቷል።››

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ሁለተኛ፦ የአላህን (ሱ.ወ.) ብያኔዎች በእሺታ፣ በትግበራና በአፈጻጸም መቀበል፣ አንድንም የአላህ ውሳኔና ሕግ እምቢ አለማለት ነው። ከአላህ ብያኔዎች (አሕካም) ውስጥ አንድም ነገር አለመቀበልና እምቢ ማለት ከአላህ (ሱ.ወ.) ጋር በሚኖረው ግንኙነት ያልተገባ አደብና መጥፎ ስነምግባር ማራመድ ማለት ነው። ለዚህም ነው የራሳችንን አስተያየትና ግላዊ ዝንባሌያችንን ከአላህ ንግግርና ከሕግጋቱ እንዳናስቀድም አላህ (ሱ.ወ.) የከለከለው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تُقَدِّمُواْ بَيۡنَ يَدَيِ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌ عَلِيمٞ ١} [الحجرات: ١].

‹‹እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው ፊት (ነፍሶቻችሁን) አታስቀድሙ፤ አላህንም ፍሩ፤ አላህ ሰሚ ዐዋቂ ነውና።››[አልሑጁራት፡1]

ሦስተኛ፦ ፍርድና ውሳኔዎቹን በውዴታና በትዕግስት መቀበል። ቀዳእና ቀደሩን በተመለከተ ከአላህ ጋር የሚኖረው አደብና መልካም ስነምግባር፣ አንድ ሰው ውሳኔውን በውዴታ ያለማጉረምረም መቀበል፣ ለቀዷእና ለቀደሩ እጅ ሰጥቶ በእርካታ መውሰድ ነው። ለዚህ ነው አላህ (ሱ.ወ.) ታጋሾችን ያሞገሰው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَبَشِّرِ ٱلصَّٰبِرِينَ ١٥٥ ٱلَّذِينَ إِذَآ أَصَٰبَتۡهُم مُّصِيبَةٞ قَالُوٓاْ إِنَّا لِلَّهِ وَإِنَّآ إِلَيۡهِ رَٰجِعُونَ ١٥٦} [البقرة: ١٥٥-١٥٦].

‹‹ታጋሾችንም (በገነት) አብስር። እነዚያን መከራ በነካቻቸው ጊዜ፣ እኛ ለአላህ ነን፣ እኛም ወደርሱ ተመላሾች ነን፣ የሚሉትን፣ (አብስር)።››[አልበቀራህ፡155-156]

ከሰዎች ጋር የሚኖር ግንኙነትን የሚመለከት መልካም ስነምግባር፦

አላህ (ሱ.ወ.) ለሰዎች ሁሉ በተለይ ደግሞ ለወላጆች፣ ለቅርብ ዘመዶችና ለጎረቤቶች ደግ መሆንን አሏል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذۡ أَخَذۡنَا مِيثَٰقَ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ لَا تَعۡبُدُونَ إِلَّا ٱللَّهَ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَانٗا وَذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَٱلۡيَتَٰمَىٰ وَٱلۡمَسَٰكِينِ وَقُولُواْ لِلنَّاسِ حُسۡنٗا وَأَقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُواْ ٱلزَّكَوٰةَ ثُمَّ تَوَلَّيۡتُمۡ إِلَّا قَلِيلٗا مِّنكُمۡ وَأَنتُم مُّعۡرِضُونَ ٨٣} [البقرة: ٨٣]،

‹‹የእስራኤል ልጆችንም ጥብቅ ኪዳን፦ አላህን እንጅ ሌላን አታምልኩ፤ በወላጆችም በግንን ሥራ (አድርጉ)፤ በዝምድና ባለ ቤቶችም፣ በየቲሞችም (አባት በሌላቸው ልጆች)፣ በምስኪኖችም፣ (በጎ ዋሉ)፤ ለሰዎችም መልካምን ተናገሩ፤ ሶላትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ፣ በማለት በያዝንባቸው ጊዜ (አስታውሱ)፤ ከዚያም ከናንተ ጥቂቶች ሲቀሩ ሸሻችሁ፤ እናንተም (ኪዳንን) የምትተው ናችሁ።››[አልበቀራህ፡83]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَّيۡسَ ٱلۡبِرَّ أَن تُوَلُّواْ وُجُوهَكُمۡ قِبَلَ ٱلۡمَشۡرِقِ وَٱلۡمَغۡرِبِ وَلَٰكِنَّ ٱلۡبِرَّ مَنۡ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةِ وَٱلۡكِتَٰبِ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ وَءَاتَى ٱلۡمَالَ عَلَىٰ حُبِّهِۦ ذَوِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَٱلۡيَتَٰمَىٰ وَٱلۡمَسَٰكِينَ وَٱبۡنَ ٱلسَّبِيلِ وَٱلسَّآئِلِينَ وَفِي ٱلرِّقَابِ وَأَقَامَ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتَى ٱلزَّكَوٰةَ وَٱلۡمُوفُونَ بِعَهۡدِهِمۡ إِذَا عَٰهَدُواْۖ وَٱلصَّٰبِرِينَ فِي ٱلۡبَأۡسَآءِ وَٱلضَّرَّآءِ وَحِينَ ٱلۡبَأۡسِۗ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ صَدَقُواْۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُتَّقُونَ ١٧٧} [البقرة: ١٧٧]،

‹‹መልካም ሥራ፣ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አግጣጫ ማዞር አይደለም፤ ግን መልካም ሥራ፣ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም ያመነ ሰው፣ ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለ ቤቶችና ለየቲሞች፣ ለሚስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንቡን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ፣ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፤ በችግር፣ በበሽታና በጦር ጊዜም ታጋሾችን (እናወድሳለን)፤ እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው፤ እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው።››[አልበቀራህ፡177]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَسۡـَٔلُونَكَ مَاذَا يُنفِقُونَۖ قُلۡ مَآ أَنفَقۡتُم مِّنۡ خَيۡرٖ فَلِلۡوَٰلِدَيۡنِ وَٱلۡأَقۡرَبِينَ وَٱلۡيَتَٰمَىٰ وَٱلۡمَسَٰكِينِ وَٱبۡنِ ٱلسَّبِيلِۗ وَمَا تَفۡعَلُواْ مِنۡ خَيۡرٖ فَإِنَّ ٱللَّهَ بِهِۦ عَلِيمٌ ٢١٥} [البقرة: ٢١٥]،

‹‹ምንን (ለማን) እንደሚለግሱ ጠይቁሃል፤ ከመልካም ነገር የምትለግሱት፣ ለወላጆችና ለቅርብ ዘመዶች፣ ለየቲሞችም፣ ለድኾችም፣ ለመንገደኞችም ነው፤ ከበጎ ነገርም ማንኛውንም ብትሠሩ አላህ እርሱን ዐዋቂ ነው በላቸው።››[አልበቀራህ፡215]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَهَاجَرُواْ وَجَٰهَدُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ وَٱلَّذِينَ ءَاوَواْ وَّنَصَرُوٓاْ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ حَقّٗاۖ لَّهُم مَّغۡفِرَةٞ وَرِزۡقٞ كَرِيمٞ ٧٤ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مِنۢ بَعۡدُ وَهَاجَرُواْ وَجَٰهَدُواْ مَعَكُمۡ فَأُوْلَٰٓئِكَ مِنكُمۡۚ وَأُوْلُواْ ٱلۡأَرۡحَامِ بَعۡضُهُمۡ أَوۡلَىٰ بِبَعۡضٖ فِي كِتَٰبِ ٱللَّهِۗ إِنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمُۢ ٧٥} [الأنفال: ٧٤- ٧٥]،

‹‹እነዚያም ያመኑና የተሰደዱ፣ በአላህም መንገድ ላይ የታገሉ፣ እነዚያም ያስጠጉና የረዱ፣ እነዚያ እነሱ በውነት አማኞች ናቸው፤ ለነሱም ምሕረትና የከበረ ሲሳይ አላቸው። እነዚያም በኋላ ያመኑና የተሰደዱ፣ ከናንተም ጋር ኾነው የታገሉ፣ እነዚያ ከናንተው ናቸው፤ የዝምድናዎች ባለቤቶችም በአላህ መጽሐፍ ከፊሎቻቸው በከፊሉ (መውረስ) የተገቡ ናቸው፤ አላህ በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው።››[አልአንፋል፡74-75]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَلَا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـٔٗاۖ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَٰنٗا وَبِذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَٱلۡيَتَٰمَىٰ وَٱلۡمَسَٰكِينِ وَٱلۡجَارِ ذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَٱلۡجَارِ ٱلۡجُنُبِ وَٱلصَّاحِبِ بِٱلۡجَنۢبِ وَٱبۡنِ ٱلسَّبِيلِ وَمَا مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُكُمۡۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ مَن كَانَ مُخۡتَالٗا فَخُورًا ٣٦} [النساء: ٣٦]،

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ናቸውና፤ ሰይጣንም ለጌታው ብርቱ ከሓዲ ነው። ከጌታህም የምትከጅላትን ጸጋ ለማጣት፤ ከነርሱ ብትዞር፤ ለነርሱ ልዝብን ቃል ተናገራቸው።››[አልኢስራእ:28]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَـَٔاتِ ذَا ٱلۡقُرۡبَىٰ حَقَّهُۥ وَٱلۡمِسۡكِينَ وَٱبۡنَ ٱلسَّبِيلِۚ ذَٰلِكَ خَيۡرٞ لِّلَّذِينَ يُرِيدُونَ وَجۡهَ ٱللَّهِۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ٣٨}[الروم: ٣٨]،

‹‹የዝምድናን ባለቤት ተገቢውን ስጠው፤ ለድኻም፤ (እርዳ)፤ ይህ ለነዚያ የአላህን ፊት (ውዴታውን) ለሚሹ መልካም ነው፤ እነዚያም እነሱ የፈለጉትንየሚገኙ ናቸው።››[አልሩም:38]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱتَّقُواْ رَبَّكُمُ ٱلَّذِي خَلَقَكُم مِّن نَّفۡسٖ وَٰحِدَةٖ وَخَلَقَ مِنۡهَا زَوۡجَهَا وَبَثَّ مِنۡهُمَا رِجَالٗا كَثِيرٗا وَنِسَآءٗۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ ٱلَّذِي تَسَآءَلُونَ بِهِۦ وَٱلۡأَرۡحَامَۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلَيۡكُمۡ رَقِيبٗا ١}[النساء: ١]،

‹‹እላንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን፤ ከርስዋም መቀናጆዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን፤ ከነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶችን የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ። ያንንም በርሱ የምትጠየቁበትን አላህንና ዝምድናዎቻችሁንም (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ፤ አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና።››[አልኒሳእ:1]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَهَلۡ عَسَيۡتُمۡ إِن تَوَلَّيۡتُمۡ أَن تُفۡسِدُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَتُقَطِّعُوٓاْ أَرۡحَامَكُمۡ ٢٢}[محمد: ٢٢]،

‹‹ብትሽሾሙም በምድር ላይ ማበላሸትን፤ ዝምድናችሁንም መቁረጥን፤ ከጀላችሁን?››[ሙሐመድ:22]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَفَمَن يَعۡلَمُ أَنَّمَآ أُنزِلَ إِلَيۡكَ مِن رَّبِّكَ ٱلۡحَقُّ كَمَنۡ هُوَ أَعۡمَىٰٓۚ إِنَّمَا يَتَذَكَّرُ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ١٩ ٱلَّذِينَ يُوفُونَ بِعَهۡدِ ٱللَّهِ وَلَا يَنقُضُونَ ٱلۡمِيثَٰقَ ٢٠ وَٱلَّذِينَ يَصِلُونَ مَآ أَمَرَ ٱللَّهُ بِهِۦٓ أَن يُوصَلَ وَيَخۡشَوۡنَ رَبَّهُمۡ وَيَخَافُونَ سُوٓءَ ٱلۡحِسَابِ ٢١ وَٱلَّذِينَ صَبَرُواْ ٱبۡتِغَآءَ وَجۡهِ رَبِّهِمۡ وَأَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَأَنفَقُواْ مِمَّا رَزَقۡنَٰهُمۡ سِرّٗا وَعَلَانِيَةٗ وَيَدۡرَءُونَ بِٱلۡحَسَنَةِ ٱلسَّيِّئَةَ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ عُقۡبَى ٱلدَّارِ ٢٢ جَنَّٰتُ عَدۡنٖ يَدۡخُلُونَهَا وَمَن صَلَحَ مِنۡ ءَابَآئِهِمۡ وَأَزۡوَٰجِهِمۡ وَذُرِّيَّٰتِهِمۡۖ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ يَدۡخُلُونَ عَلَيۡهِم مِّن كُلِّ بَابٖ ٢٣ سَلَٰمٌ عَلَيۡكُم بِمَا صَبَرۡتُمۡ فَنِعۡمَ عُقۡبَى ٱلدَّارِ ٢٤ وَٱلَّذِينَ يَنقُضُونَ عَهۡدَ ٱللَّهِ مِنۢ بَعۡدِ مِيثَٰقِهِۦ وَيَقۡطَعُونَ مَآ أَمَرَ ٱللَّهُ بِهِۦٓ أَن يُوصَلَ وَيُفۡسِدُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمُ ٱللَّعۡنَةُ وَلَهُمۡ سُوٓءُ ٱلدَّارِ ٢٥}[الرعد: ١٩ـ ٢٥].

‹‹እርሱ ከጌታህ ወዳንተ የተወረደው እውነት መኾኑን የሚያውቅ ሰው፤ እንደዚያ እርሱ ዕውር እንደ ኾነው ሰው ነውን? የሚገሠጹት የአእምሮ ባለ ቤቶች ብቻ ናቸው። እነዚያ በአላህ ቃል ኪዳን የሚሞሉ፤ የጠበቀውንም ኪዳን የማያፈርሱ ናቸው። እነዚያም አላህ እንዲቀጠል በርሱ ያዘዘውን ነገር የሚቀጥሉ፤ ጌታቸውንም የሚያከብሩ፤ መጥፎንም ቁጥጥር የሚፈሩ ናቸው። እነዚያም የጌታቸውን ውዴታ ለመፈለግ የታገሡ፤ ሶላትንም አዘውትረው የሰገዱ፤ እኛ ከሰጠናቸው ሲሳይም በምስጢርም ኾነ በግልጽ የመጸወቱ፤ ክፉውንም ነገር በበጎ የሚገፉትሩ ናቸው፤ እነዚያ ለነሱ መጨረሻይቱ ምስጉን አገር አለቻቸው። (እርሷም) የመኖሪያ

‹‹አላህንም ተገዙ፤ በርሱም ምንንም አታጋሩ፤ በወላጆችና በቅርብ ዝምድና ባለቤትም፤ በየቲሞችም፤ በምስኪኖችም፤ በቅርብ ጎረቤትም፤ በሩቅ ጎረቤትም፤ በጎን ባልደረባም፤ በመንገደኛም፤ እጆቻችሁም ንብረት ባደረጓቸው (ባሮች)፤ መልካምን (ሥሩ)፤ አላህ ኩራተኛ ጉረኛ የኾነን ሰው አይወድምና።››[አልኒሳእ:36]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱللَّهَ يَأۡمُرُ بِٱلۡعَدۡلِ وَٱلۡإِحۡسَٰنِ وَإِيتَآيِٕ ذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَيَنۡهَىٰ عَنِ ٱلۡفَحۡشَآءِ وَٱلۡمُنكَرِ وَٱلۡبَغۡيِۚ يَعِظُكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ ٩٠}
[النحل: ٩٠]

‹‹አላህ በማስተካከል፤ በማላመርም፤ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል፤ ከአስከፊም፤ (ከማመንዘር)፤ ከሚጠላም ነገር ሁሉ፤ ከመበደልም ይከለክላል፤ ትገነዘቡ ዘንድ፤ ይገሥጻችኋል።››[አልነሕል:90]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَقَضَىٰ رَبُّكَ أَلَّا تَعۡبُدُوٓاْ إِلَّآ إِيَّاهُ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَٰنًاۚ إِمَّا يَبۡلُغَنَّ عِندَكَ ٱلۡكِبَرَ أَحَدُهُمَآ أَوۡ كِلَاهُمَا فَلَا تَقُل لَّهُمَآ أُفّٖ وَلَا تَنۡهَرۡهُمَا وَقُل لَّهُمَا قَوۡلٗا كَرِيمٗا ٢٣ وَٱخۡفِضۡ لَهُمَا جَنَاحَ ٱلذُّلِّ مِنَ ٱلرَّحۡمَةِ وَقُل رَّبِّ ٱرۡحَمۡهُمَا كَمَا رَبَّيَانِي صَغِيرٗا ٢٤ رَّبُّكُمۡ أَعۡلَمُ بِمَا فِي نُفُوسِكُمۡۚ إِن تَكُونُواْ صَٰلِحِينَ فَإِنَّهُۥ كَانَ لِلۡأَوَّٰبِينَ غَفُورٗا ٢٥ وَءَاتِ ذَا ٱلۡقُرۡبَىٰ حَقَّهُۥ وَٱلۡمِسۡكِينَ وَٱبۡنَ ٱلسَّبِيلِ وَلَا تُبَذِّرۡ تَبۡذِيرًا ٢٦ إِنَّ ٱلۡمُبَذِّرِينَ كَانُوٓاْ إِخۡوَٰنَ ٱلشَّيَٰطِينِۖ وَكَانَ ٱلشَّيۡطَٰنُ لِرَبِّهِۦ كَفُورٗا ٢٧ وَإِمَّا تُعۡرِضَنَّ عَنۡهُمُ ٱبۡتِغَآءَ رَحۡمَةٖ مِّن رَّبِّكَ تَرۡجُوهَا فَقُل لَّهُمۡ قَوۡلٗا مَّيۡسُورٗا ٢٨}[الإسراء: ٢٣ـ ٢٨]،

‹‹ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፦ እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፤ በወላጆቻችሁም መልካምን ሥሩ፤ በአንተ ዘንድ ኾነው፤ አንዳቸው ወይም ሁለታቸው፤ እርጅናን ቢደርሱ፤ ፍህ አትበላቸው፤ አትገላምጣቸውም፤ ለነርሱም መልካምን ቃል ተናገራቸው። ለሁለቱም ከእዝነትህ የመዋረድን ክንፍ ዝቅ አድርግላቸው፤ ጌታዬ ሆይ! በሕጻንነቱ (በርኅራሄ) እንዳሳደጉኝ፤ እዘንላቸውም በል። ጌታችሁ በነፍሶቻችሁ ውስጥ ያለውን ሁሉ ዐዋቂ ነው። ታዛገሮችም ብትኾኑ፤ (በመሳሳትም ብታጠፉ) እርሱ ለተመላሾች መሓሪ ነው። ለዝምድና ባለቤትም መብቱን ስጥ፤ ለምስኪንና ለመንገደኛም (ስጥ)፤ ማባከንንም አታባክን። አባካኞች የሰይጣናት ወንድሞች

ገነቶች ናት፤ይገቡባታል፤ከአባቶቻቸውም ከዝርያቸውም መልካም የሠራ ሰው፣(ይገባታል)፤መላእክትም በነሱ ላይ ከየደጃፉ ሁሉ ይገባሉ። ሰላም ለናንተ ይኹን፣(ይህ ምንዳ) በመታገሣችሁ ነው፣የመጨረሻይቱም አገር ምን ታምር! (ይሏቸዋል)። እነዚያም የአላህን ኪዳን ከጠበቀ በኋላ የሚያፈርሱ፣አላህም እንዲቀጠል በርሱ ያዘዘውን ነገር የሚቆርጡ፣በምድርም ላይ የሚያበላሹ፣እነዚያ ለነሱ ርግማን አለባቸው፤ለነሱም መጥፎ አገር (ገሀነም) አላቸው።››[አልረዕድ፡ 19-25]

መልካም ስነ ምግባር እስላም ውስጥ ከወዳጅ፣ከጓደኛ ከዘመድና ከጎረቤት ጋር በሚኖር ግንኙነት ላይ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፣ደመኛ ተዋጊ ቢሆን እንኳ ወደ ጠላትም ጭምር ይሸጋገራል! በዚህም መላውን የሰው ዘር ያካትታል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تَسْتَوِي ٱلْحَسَنَةُ وَلَا ٱلسَّيِّئَةُۚ ٱدْفَعْ بِٱلَّتِي هِيَ أَحْسَنُ فَإِذَا ٱلَّذِي بَيْنَكَ وَبَيْنَهُۥ عَدَٰوَةٌ كَأَنَّهُۥ وَلِيٌّ حَمِيمٌ ٣٤} [فصلت: ٣٤].

‹‹መልካሚቱና ክፉይቱም (ጠባይ) አይተካከሉም፤በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ጠባይ (መጥፎይቱን) ገፍትር፤ያን ጊዜ ያ ባንተና በርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው፣እርሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይኾናል።››[ሓ ሚም አልሰጅዳህ፡34]

እኛን በመዋጋት ላይ ከሚገኙት ጋር እንኳ ቢሆን ወሰን እንዳናልፍ ሲያዘን አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَقَٰتِلُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ ٱلَّذِينَ يُقَٰتِلُونَكُمْ وَلَا تَعْتَدُوٓاْۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ ٱلْمُعْتَدِينَ ١٩٠} [البقرة: ١٩٠]،

‹‹እነዚያንም የሚጋደሏችሁን (ከሓዲዎች)፣በአላህ መንገድ ተጋደሉ፤ወሰንንም አተለፉ፤አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና።››[አልበቀራህ፡190]

ከተዋጊ ጠላት ጋር እንኳ ቢሆን እስላም የሚከተለውን መልካም ስነምግባር፣ጠላትን ለመዋጋት በአላህ መንገድ ለመታገል ለጅሃድ ለተሰማራው ጦራቸው ነቢዩ ﷺ በሰጡት ትእዛዞች ውስጥ እንመልከት። ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ቃል ኪዳን አታፈርሱ፤ምርኮን አትደብቁ፣አታሰቃዩ (አካላዊ ሰቆቃ አታድርሱ)፤ልጆችንም፣የገዳማት ሰዎችንም አትግደሉ።›› [በአሕመድ የተዘገበ] በተዋጊ ጠላቶች አያያዝ ላይ እንዲህ ያለውን መልካም ስነምግባር የሚያዝ ሃይማኖት ነገር በጣም አስገራሚ ነው። ተዋጊ ያልሆኑትን በሚመለከትም - ጠላት እንኳ ቢሆን - ለነሱ ደግና ፍትሐዊ መሆንን ሲያበረታታ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَّا يَنْهَىٰكُمُ ٱللَّهُ عَنِ ٱلَّذِينَ لَمْ يُقَٰتِلُوكُمْ فِي ٱلدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُم مِّن دِيَٰرِكُمْ أَن تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوٓاْ إِلَيْهِمْۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلْمُقْسِطِينَ ٨} [الممتحنة: ٨].

‹‹ከነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ፣ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሃዲዎች)፣መልካም ብትውሉላቸውና ወደነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፤አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና።››[አልሙምተሒናህ፡8]

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

በእንስሳት አያያዝ ላይ የሚኖር መልካም ስነምግባር

እስላም ውስጥ መልካም ስነምግባር እንስሳትንም እስከማካተት ድረስ የሰፋ ነው። የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹አንዲት ሴት አስክትሞት ባሰረቻት ድመት ምክንያት ተቀጣች፤ በዚያ ምክንያትም እሳት ገባች። ስታስራት አልመገበቻትም፣ አላጠጣቻትምም፣ ወይም የመሬት ነፍሳትንና ትላትል ትበላ ዘንድ ፈታ አልለቀቀቻትም።›› [በቡኻሪ የተዘገበ] አላህ (ሱ.ወ.) በእንስሳት አስተራረድ እንኳ ደግነትና ርኅራሄን አሏል። ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹አላህ በሁሉም ነገሮች ላይ ደግ መሥራትን ወስኗል፤ እናም ስትገድሉ አገዳደልን አሳምሩ፤ ስታርዱም አስተራረድን አሳምሩ፤ አንዳችሁ (ሲያርድ) ቢላውን ይሞርድ፣ የሚታረደውን እንስሳም (ቶሎ እንዲሞት በማድረግ) ያሳርፈው።›› [በሙስሊም የተዘገበ]

ምእመናን ወንድማማቾች ናቸው

‹‹በእስላም ውስጥ የሁሉንም ምእመናን ወንድማማችነትን ዒላማ ያደረገው ታላቅ ምሳሌ፤ ሰዎችን ወደዚህ እምነት በኃል ከሚስቡ ምክንያቶች አንዱ ነው።››

ቶማስ አርኖልድ

እንግሊዛዊ ኦሪየንታሊስት

ተፈጥሮና አካባቢ ጥበቃን የሚመለከት መልካም ስነምግባር

በተመሳሳይ መልኩም እስላም ለተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃና ለአጠቃላይ ትእይንት እንክብካቤም ሳይቀር መልካም ስነምግባርን ይዞ መጥቷል። ማበከንን በማውገዝ የተፈጥሮ ሀብቶችን ማራቆትና ማበላሸት እንዲቆም ጥሪ አድርጓል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{كُلُواْ وَٱشۡرَبُواْ مِن رِّزۡقِ ٱللَّهِ وَلَا تَعۡثَوۡاْ فِي ٱلۡأَرۡضِ مُفۡسِدِينَ ٦٠} [البقرة: ٦٠]،

‹‹ከአላህ ሲሳይ ብሉ፤ ጠጡም፤ አመጠኞችም ኾናችሁ በምድር ላይ አታበላሹ (አልናችሁ)።››[አልበቀራህ:60]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تُطِيعُوٓاْ أَمۡرَ ٱلۡمُسۡرِفِينَ ١٥١ ٱلَّذِينَ يُفۡسِدُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَا يُصۡلِحُونَ ١٥٢} [الشعراء: ١٥١-١٥٢]،

‹‹የወሰን አላፊዎችንም ትዕዛዝ አትከተሉ፤ የነዚያን በምድር ላይ የሚያጠፉትንና የማያበጁትን።› [አልሹዐራእ:151-152]

ውሃና የተቀሩትን ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶችን በተመለከተም እስላም ታላቅ ትኩረት ሰጥቷል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَوَ لَمۡ يَرَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَنَّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ كَانَتَا رَتۡقٗا فَفَتَقۡنَٰهُمَاۖ وَجَعَلۡنَا مِنَ ٱلۡمَآءِ كُلَّ شَيۡءٍ

حَيٍّۚ أَفَلَا يُؤۡمِنُونَ ٣٠} [الأنبياء: ٣٠]،

‹‹እነዚያም የካዱት ሰማያትና ምድር የተጣበቁ የነበሩና የለያየናቸው መኾናችንን አያውቁምን? ሕያው የኾነንም ሁሉ ከውሃ ፈጠርን፤ አያምኑምን?››[አልአንቢያ: 30]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱللَّهُ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَحۡيَا بِهِ ٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ مَوۡتِهَآۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لِّقَوۡمٖ يَسۡمَعُونَ ٦٥} [النحل: ٦٥].

‹‹አላህም ከሰማይ ውሃን አወረደ፤ በርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው አደረገ፤ በዚህ ውስጥ ለሚሰሙ ሕዝቦች በእርግጥ ታምር አለ።››[አልነሕል:65]

ከቅዱስ ቁርኣን ጎን ለጎን፣ ነቢዩም ﷺ በፊናቸው ለአካባቢ ጥበቃና ለተፈጥሮ ሀበት እንክብካቤ ጥሪ ያደረጉ ሲሆን፣ ነቢያዊው ሱንና የአፈር መሸርሸር፣ የበረሃማነትና የድርቅ ተፈጥሯዊ አደጋዎች እንዳይከሰቱ ለአካባቢ ጥበቃ በተደጋጋሚ ጥሪ በሚያደርጉ ሐዲሶች የተሞላ ነው። ይህን በማስመልከትም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ሦስቱን መርገምት ተጠንቀቁ፦ በውሃ መውረጃዎች (በር) በመንገድ ላይና (ሰው በሚያርፍበት) ጥላ በታ መጸዳዳት ናቸው።›› [በአቡ ዳውድ የተዘገበ] በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ማንኛውም ሙስሊም ዘር ዘርቶ ወይም ችግኝ ተክሎ፣ ወፍ ሰው ወይም እንስሳ ከተክሉ ቢበላ ሶደቃ ይሆንለታል።›› [በሙስሊም የተዘገበ] እንደዚሁም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ትንሳኤ ቀን ቢጆምርና በእንዳችሁ እጅ ችግኝ ቢኖር፣ ከመነሳቱ በፊት ሊተክለው ከቻለ ይድርግ።›› [በአሕመድ የተዘገበ] የአላህ መልክተኛ ﷺ ሰዐድ ውዱእ ሲያደርጉ በአጠገባቸው አለፉና፦ ‹‹ይሕ ብክነት ምንድነው?›› አሏቸው። ሰዐድም ‹‹በውዱእም ማባከን አለ እንዴ?›› ሲሉ ጠየቁ። ነቢዩም ﷺ ፦ ‹‹አዎ፣ በሚፈስ ውሃ ላይ ብትሆንም እንኳ።›› አሉ። [በኢብንማጃህ የተዘገበ] ይህ በጦርነት ጊዜ ለተታዩትም በማዋጉበት ወቅት እንኳ ሳይቀር የነቢዩ ﷺ ባልደረቦች አካባቢ

እስላምና አካባቢ ጥበቃ

‹‹ቅዱስ ቁርኣን ውስጥ በሰው ልጅና በተፈጥሮ መካከል የሚለይ ነገር የለም። የሙስሊሙ ዓለም ለሰው ልጅ የቀረበ የተከማቸ የጥበብና የዕውቀት ታላቅ እምቅ ሀብት ባለቤት ነው።››

ልዑል ቻርልዝ

የእንግሊዝ አልጋ ወራሽ

https://www.path-2-happiness.com/am

ጥበቃን አስመልክተው ይከተሉት የነበረው መልካም ስነምግባር ነው። አቡ በክር ለጦርነት ላሰማሩት ጦር አዛዥ የሚከተለውን መመሪያ ሰጥተዋል፦ ‹‹ሕጻን አትግደል፤ ሴትም፤ አዘውንት ሽማግሌም። የሚያፈራ ዛፍም አትቁረጥ፤ ፍየልም ሆነ ላም ለመብላት ካልሆነ በስተቀር አትግደል። ቤቶችን አታፈርስ፤ የተምር ዛፍን አታጥለቀልቅ፣ አታቃጥለውም።›› [በአሕመድ የተዘገበ

ከመልካም ስነምግባር ትእዛዛት መካከል፦

እዚህ ላይ በአላህ መጽሐፍና በነቢዩ ﷺ ሱንና ውስጥ ከቀረቡት የመልካም ስነምግባር ትእዛዛት መካከል የተወሰኑትን መመልከቱ ጥሩ ይሆናል። ከነዚህ መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፦

ቅዱስ ቁርኣን ውስጥ፦

- አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱللَّهَ يَأۡمُرُكُمۡ أَن تُؤَدُّواْ ٱلۡأَمَٰنَٰتِ إِلَىٰٓ أَهۡلِهَا وَإِذَا حَكَمۡتُم بَيۡنَ ٱلنَّاسِ أَن تَحۡكُمُواْ بِٱلۡعَدۡلِۚ إِنَّ ٱللَّهَ نِعِمَّا يَعِظُكُم بِهِۦٓۗ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ سَمِيعَۢا بَصِيرٗا ٥٨} [النساء: ٥٨].

‹‹አላህ አደራዎችን ወደ ባለቤቶቻቸው፤ እንድታደርሱ ያዛችኋል። በሰዎችም መካከል በፈረዳችሁ ጊዜ፤ በትክክል እንድትፈርዱ፤ (ያዛችኋል)፤ አላህ በርሱ የሚገሥጻችሁ ነገር ምን ምር! አላህ ሰሚ ተመልካች ነው።››[አልኒሳእ፡58]

- በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ تَعَالَوۡاْ أَتۡلُ مَا حَرَّمَ رَبُّكُمۡ عَلَيۡكُمۡۖ أَلَّا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـٔٗاۖ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَٰنٗاۖ وَلَا تَقۡتُلُوٓاْ أَوۡلَٰدَكُم مِّنۡ إِمۡلَٰقٖ نَّحۡنُ نَرۡزُقُكُمۡ وَإِيَّاهُمۡۖ وَلَا تَقۡرَبُواْ ٱلۡفَوَٰحِشَ مَا ظَهَرَ مِنۡهَا وَمَا بَطَنَۖ وَلَا تَقۡتُلُواْ ٱلنَّفۡسَ ٱلَّتِي حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ ١٥١ وَلَا تَقۡرَبُواْ مَالَ ٱلۡيَتِيمِ إِلَّا بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ حَتَّىٰ يَبۡلُغَ أَشُدَّهُۥۚ وَأَوۡفُواْ ٱلۡكَيۡلَ وَٱلۡمِيزَانَ بِٱلۡقِسۡطِۖ لَا نُكَلِّفُ نَفۡسًا إِلَّا وُسۡعَهَاۖ وَإِذَا قُلۡتُمۡ فَٱعۡدِلُواْ وَلَوۡ كَانَ ذَا قُرۡبَىٰۖ وَبِعَهۡدِ ٱللَّهِ أَوۡفُواْۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ ١٥٢ وَأَنَّ هَٰذَا صِرَٰطِي مُسۡتَقِيمٗا فَٱتَّبِعُوهُۖ وَلَا تَتَّبِعُواْ ٱلسُّبُلَ فَتَفَرَّقَ بِكُمۡ عَن سَبِيلِهِۦۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ١٥٣} [الأنعام: ١٥١-١٥٣].

‹‹ኑ፤ ጌታችሁ በናንተ ላይ እርም ያደረገውን ነገር (በርሱም ያዘዛችሁን) ላንብባላችሁ በላቸው፤ በርሱ (በአላህ) ምንንም ነገር አታጋሩ፤ ለወላጆችም በጎን ሥራ (ሥሩ)፤ ልጆቻችሁንም ከድኽነት ፍራቻ አትግደሉ፤ እኛ እናንተንም እነርሱንም እንመግባችኋለንና፤ መጥፎ ሥራዎችንም ከርሷ የተገለጸውንም የተደበቀውንም ሁሉ አትቅረቡ፤ ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ በሕግ ቢኾን እንጅ አትግደሉ፤ ይኻችሁ ታውቁ ዘንድ (አላህ) በርሱ አዘዛችሁ። የየቲምንም ገንዘብ፤ ብርታቱን (አካለ መጠን) እስኪደርስ ድረስ በዚያች እርሷ መልካም በኾነች ኹኔታ እንጂ አትቅረቡ፤ ስፍርንና ሚዛንንም በትክክል ሙሉ፤ ነፍስን ችሎታዋን እንጂ አናስገድድም፤ በተናጋራችሁም ጊዜ፤ በዘመዶቻችሁ ላይ ቢኾንም እንኳ፤ (እውነትን በመናገር) አስተካክሉ፤ በአላህም ቃል ኪዳን ሙሉ፤ ይኻችሁ ትገሠጹ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ። ይህም ቀጥተኛ ሲኾን መንገዴ

ነው፤ ተከተሉትም፤ (የጥመት) መንገዶችንም አትከተሉ፤ ከ(ቀጥተኛው) መንገዱ እናንተን ይለያዩዋችኋልና። ይኻችሁ ትጠነቀቁ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ።››[አልአንዓም፡ 151-153]

- በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تُفۡسِدُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ بَعۡدَ إِصۡلَٰحِهَا وَٱدۡعُوهُ خَوۡفٗا وَطَمَعًاۚ إِنَّ رَحۡمَتَ ٱللَّهِ قَرِيبٞ مِّنَ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ٥٦} [الأعراف: ٥٦].

‹‹በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ፤ ፈርታችሁና ከጅላችሁም ተገዙት፤ የአላህ ችሮታ ከበጎ አድራጊዎች ቅርብ ነውና።››[አልአዕራፍ፡56]

- በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱصۡبِرۡ فَإِنَّ ٱللَّهَ لَا يُضِيعُ أَجۡرَ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ١١٥} [هود: ١١٥].

‹‹ታገሥም፤ አላህ የበጎ ሠሪዎችን ምንዳ አያጠፋምና።››[ሁድ፡115]

- በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تَجۡعَلۡ يَدَكَ مَغۡلُولَةً إِلَىٰ عُنُقِكَ وَلَا تَبۡسُطۡهَا كُلَّ ٱلۡبَسۡطِ فَتَقۡعُدَ مَلُومٗا مَّحۡسُورًا ٢٩ إِنَّ رَبَّكَ يَبۡسُطُ ٱلرِّزۡقَ لِمَن يَشَآءُ وَيَقۡدِرُۚ إِنَّهُۥ كَانَ بِعِبَادِهِۦ خَبِيرَۢا بَصِيرٗا ٣٠ وَلَا تَقۡتُلُوٓاْ أَوۡلَٰدَكُمۡ خَشۡيَةَ إِمۡلَٰقٖۖ نَّحۡنُ نَرۡزُقُهُمۡ وَإِيَّاكُمۡۚ إِنَّ قَتۡلَهُمۡ كَانَ خِطۡـٔٗا كَبِيرٗا ٣١ وَلَا تَقۡرَبُواْ ٱلزِّنَىٰٓۖ إِنَّهُۥ كَانَ فَٰحِشَةٗ وَسَآءَ سَبِيلٗا ٣٢ وَلَا تَقۡتُلُواْ ٱلنَّفۡسَ ٱلَّتِي حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۗ وَمَن قُتِلَ مَظۡلُومٗا فَقَدۡ جَعَلۡنَا لِوَلِيِّهِۦ سُلۡطَٰنٗا فَلَا يُسۡرِف فِّي ٱلۡقَتۡلِۖ إِنَّهُۥ كَانَ مَنصُورٗا ٣٣ وَلَا تَقۡرَبُواْ مَالَ ٱلۡيَتِيمِ إِلَّا بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ حَتَّىٰ يَبۡلُغَ أَشُدَّهُۥۚ وَأَوۡفُواْ بِٱلۡعَهۡدِۖ إِنَّ ٱلۡعَهۡدَ كَانَ مَسۡـُٔولٗا ٣٤ وَأَوۡفُواْ ٱلۡكَيۡلَ إِذَا كِلۡتُمۡ وَزِنُواْ بِٱلۡقِسۡطَاسِ ٱلۡمُسۡتَقِيمِۚ ذَٰلِكَ خَيۡرٞ وَأَحۡسَنُ تَأۡوِيلٗا ٣٥ وَلَا تَقۡفُ مَا لَيۡسَ لَكَ بِهِۦ عِلۡمٌۚ إِنَّ ٱلسَّمۡعَ وَٱلۡبَصَرَ وَٱلۡفُؤَادَ كُلُّ أُوْلَٰٓئِكَ كَانَ عَنۡهُ مَسۡـُٔولٗا ٣٦ وَلَا تَمۡشِ فِي ٱلۡأَرۡضِ مَرَحًاۖ إِنَّكَ لَن تَخۡرِقَ ٱلۡأَرۡضَ وَلَن تَبۡلُغَ ٱلۡجِبَالَ طُولٗا ٣٧ كُلُّ ذَٰلِكَ كَانَ سَيِّئُهُۥ عِندَ رَبِّكَ مَكۡرُوهٗا ٣٨ ذَٰلِكَ مِمَّآ أَوۡحَىٰٓ إِلَيۡكَ رَبُّكَ مِنَ ٱلۡحِكۡمَةِۗ وَلَا تَجۡعَلۡ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ فَتُلۡقَىٰ فِي جَهَنَّمَ مَلُومٗا مَّدۡحُورًا ٣٩} [الإسراء: ٢٩-٣٩].

‹‹እጅህንም ወደ አንገትህ የታሠረች አታድርግ፤ መዘርጋትንም ሁሉ አትዘርጋት፤ የተወቀስክ፤ የተቆጨህ፤ ትኾናለህና። ጌታህ ሲሳይን ለሚሻው ሰው ያሰፋል፤ ያጠባልም፤ እርሱ በባሮቹ ኹኔታ ውስጠ ዐዋቂ ተመልካች ነውና። ልጆቻችሁንም ድኽነትን ለመፍራት አትግደሉ፤ እኛ እንመግባቸዋለን፤ እናንተንም፤ (እንመግባለን)፤ እነሱን መግደል ታላቅ ኃጢአት ነውና። ዝሙትንም አትቅረቡ፤ እርሱ በእርግጥ መጥፎ ሥራ ነውና፤ መንገድነቱም ከፋ! ያችንም አላህ ያወገዛትን [መግደሏን ውጉዝ ያደረገውን] ነፍስ፤ ያለ ሕግ አትግደሉ፤ የተበደለም ኾኖ የተገደለ ሰው፤ ለዘመዱ (በገዳይ ላይ) በእርግጥ ስልጣንን አድርገናል፤ በመግደልም ወሰንን አይለፍ፤ እርሱ የተረዳ ነውና። የየቲምንም ገንዘብ፤ የብርታት ጊዜውን እስኪደርስ ድረስ በዚያች እርሷ መልካም በኾነች ኹኔታ እንጂ አትቅረቡ፤ በኪዳናችሁም ሙሉ፤ ኪዳን የሚጠየቁበት ነውና። በሰፈራችሁም ጊዜ፤ ስፍርን ሙሉ፤ በትክክለኛው ሚዛንም መዝኑ፤ ይህ መልካም ነገር ነው፤ መጨረሻውም ያማረ ነው። ለአንተም በርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ٱلْأُمُورِ ﴿١٧﴾ وَلَا تُصَعِّرْ خَدَّكَ لِلنَّاسِ وَلَا تَمْشِ فِى ٱلْأَرْضِ مَرَحًا ۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ كُلَّ مُخْتَالٍ فَخُورٍ ﴿١٨﴾ وَٱقْصِدْ فِى مَشْيِكَ وَٱغْضُضْ مِن صَوْتِكَ ۚ إِنَّ أَنكَرَ ٱلْأَصْوَٰتِ لَصَوْتُ ٱلْحَمِيرِ ﴿١٩﴾} [ሉቅማን: ١٧-١٩].

‹‹ልጄ ሆይ! ሶላትን አስተካክለህ ስገድ፤በበጎ ነገርም እዘዝ፤ከሚጠላም ሁሉ ከልክል፤በሚያገኝህም መከራ ላይ ታገሥ፤ይህ፣በምር ከሚያያዙ ነገሮች ነው። ጉንጭህንም (በኩራት) ከሰዎች አታዙር፤በምድርም ላይ ተንበጥርረህ አትሺድ፤አላህ ተንበጣራሪን፣ጉረኛን ሁሉ አይወድምና። በአካሄድህም፤መካከለኛ ኹን፤ከድምጽህም ዝቅ አድርግ፤ከድምጾች ሁሉ አስከፊው የአህዮች ድምጽ ነውና።››[ሉቅማን:19]

- በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَعِبَادُ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلَّذِينَ يَمْشُونَ عَلَى ٱلْأَرْضِ هَوْنًا وَإِذَا خَاطَبَهُمُ ٱلْجَٰهِلُونَ قَالُوا۟ سَلَٰمًا ﴿٦٣﴾} [الفرقان: ٦٣].

‹‹የአልረሕማንም ባሮች፤እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚኼዱት፤ባለጌዎችም (በክፉ) ባነጋገሩዋቸው ጊዜ፤ሰላም ሚሉት ናቸው።››[አልፉርቃን:63]

- በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا۟ بِهِۦ شَيْـًٔا ۖ وَبِٱلْوَٰلِدَيْنِ إِحْسَٰنًا وَبِذِى ٱلْقُرْبَىٰ وَٱلْيَتَٰمَىٰ وَٱلْمَسَٰكِينِ وَٱلْجَارِ ذِى ٱلْقُرْبَىٰ وَٱلْجَارِ ٱلْجُنُبِ وَٱلصَّاحِبِ بِٱلْجَنۢبِ وَٱبْنِ ٱلسَّبِيلِ وَمَا مَلَكَتْ أَيْمَٰنُكُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ مَن كَانَ مُخْتَالًا فَخُورًا ﴿٣٦﴾} [النساء: ٣٦].

‹‹አላህንም ተገዙ፤በርሱም ምንንም አታጋሩ፤በወላጆችና በቅርብ ዝምድና ባለቤትም፤በየቲሞችም፤በምስኪኖችም፤በቅርብ ጎረቤትም፤በሩቅ ጎረቤትም፤በጎን ባልደረባም፤በመንገደኛም፤እጆቻችሁም ንብረት ባደረጓቸው (ባሮች)፤መልካምን (ሥሩ)፤አላህ ኩራተኛ ጉረኛ የኾነን ሰው አይወድም።››[አልኒሳእ:36]

- በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَبِمَا رَحْمَةٍ مِّنَ ٱللَّهِ لِنتَ لَهُمْ ۖ وَلَوْ كُنتَ فَظًّا غَلِيظَ ٱلْقَلْبِ لَٱنفَضُّوا۟ مِنْ حَوْلِكَ ۖ فَٱعْفُ عَنْهُمْ وَٱسْتَغْفِرْ لَهُمْ وَشَاوِرْهُمْ فِى ٱلْأَمْرِ ۖ فَإِذَا عَزَمْتَ فَتَوَكَّلْ عَلَى ٱللَّهِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلْمُتَوَكِّلِينَ ﴿١٥٩﴾} [آل عمران: ١٥٩].

‹‹ከአላህም በኾነች ችሮታ ለዘብክላቸው። ዐመለ መጥፎ ልበ ደረቅም በኾንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር። ከነርሱም ይቅር በል። ለነርሱም ምሕረትን ለምንላቸው። በነገሩም ሁሉ አማክራቸው። ቁርጥ ሐሳብም ባደረግህ ጊዜ በአላህ ላይ ተመካ። አላህ በርሱ ላይ ተመኪዎችን ይወዳልና።››[አሊ. ዒምራን:159]

አትከተል፤መስሚያ፣ማያም፤ልብም፤እነዚህ ሁሉ (ባለቤታቸው) ከነሱ ተጠያቂ ነውና። በምድርም ላይ የተንበጣረርክ ሆነህ አትሺድ፤አንተ ፈጽሞ ምድርን አትሰረጉድምና፣በርዝመትም ፈጽሞ ጋራዎችን አትደርስምና። ይህ ሁሉ (ከሃያ አምስቱ ጠባዮች ውስጥ) መጥፎው (አስራ ሁለቱ ክልክሎች) እጌታህ ዘንድ የተጠላ ነው። ይህ ጌታህ ከጥበቡ ወደ አንተ ካወረደው ነገር ነው፤ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ አታድርግ፤የተወቀስክ፣የተባረርክ ኾነህ በገሀነም ውስጥ ትጣላለህና።››[አልኢስራእ:29-39]

- በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَسَارِعُوٓا۟ إِلَىٰ مَغْفِرَةٍ مِّن رَّبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلْأَرْضُ أُعِدَّتْ لِلْمُتَّقِينَ ﴿١٣٣﴾ ٱلَّذِينَ يُنفِقُونَ فِى ٱلسَّرَّآءِ وَٱلضَّرَّآءِ وَٱلْكَٰظِمِينَ ٱلْغَيْظَ وَٱلْعَافِينَ عَنِ ٱلنَّاسِ ۗ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿١٣٤﴾} [آل عمران: ١٣٣-١٣٤].

‹‹ከጌታችሁ ወደ ኾነችም ምሕረትና፤ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ኾነች ገነት፤አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትኾን ተቻኮሉ። ለነዚያ በድሎትም ኾነ በችግር ለሚለግሱት፤ቁጭትንም ገቺዎች፤ከሰዎችም ይቅርታ አድራጊዎች ለኾኑት (ተደግሳለች)፤አላህም በጎ ሠሪዎችን ይወዳል።››[አሊ. ዒምራን:133-134]

- በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا يَسْخَرْ قَوْمٌ مِّن قَوْمٍ عَسَىٰٓ أَن يَكُونُوا۟ خَيْرًا مِّنْهُمْ وَلَا نِسَآءٌ مِّن نِّسَآءٍ عَسَىٰٓ أَن يَكُنَّ خَيْرًا مِّنْهُنَّ ۖ وَلَا تَلْمِزُوٓا۟ أَنفُسَكُمْ وَلَا تَنَابَزُوا۟ بِٱلْأَلْقَٰبِ ۖ بِئْسَ ٱلِٱسْمُ ٱلْفُسُوقُ بَعْدَ ٱلْإِيمَٰنِ ۚ وَمَن لَّمْ يَتُبْ فَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴿١١﴾ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱجْتَنِبُوا۟ كَثِيرًا مِّنَ ٱلظَّنِّ إِنَّ بَعْضَ ٱلظَّنِّ إِثْمٌ ۖ وَلَا تَجَسَّسُوا۟ وَلَا يَغْتَب بَّعْضُكُم بَعْضًا ۚ أَيُحِبُّ أَحَدُكُمْ أَن يَأْكُلَ لَحْمَ أَخِيهِ مَيْتًا فَكَرِهْتُمُوهُ ۚ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ تَوَّابٌ رَّحِيمٌ ﴿١٢﴾ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَٰكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَىٰ وَجَعَلْنَٰكُمْ شُعُوبًا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓا۟ ۚ إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ ٱللَّهِ أَتْقَىٰكُمْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ ﴿١٣﴾} [الحجرات: ١١-١٣]

‹‹እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ወንዶች ከወንዶች አይቀልዱ፤ከነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፤ሴቶችም ከሴቶች (አይሳለቁ)፤ከነሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፤ነፍሶቻችሁንም አታነውሩ (ከፊላችሁ ከፊሉን አይዝለፍ)፤በመጥፎ ስሞችም አትጠራሩ፤ከእምነት በኋላ የማመጥ ስም ከፋ፤ያልተጸጸተም ሰው፣እነዚያ እነሱ በዳዮቹ ናቸው። እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከጥርጣሬ ብዙውን ራቁ፤ከጥርጣሬ ከፊሉ ኃጢአት ነውና፤ነውርንም አትከታተሉ፤ከፊላችሁም ከፊሉን አይማ፤አንደኛችሁ የወንድሙን ስጋ የሞተ ኾኖ ሊበላው ይወዳልን? (መብላቱን) ጠላችሁትም፤(ሐሜትንም ጥሉት)፤አላህንም ፍሩ፤አላህ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና። እላንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤እንድትተዋወቁም ጎሣዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፤አላህ ዘንድ በላጫችሁ፣በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፤አላህ ግልጽን ዐዋቂ፣ውስጥንም ዐዋቂ ነው።››[አልሑጁራት: 11-13]

- በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰبُنَىَّ أَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ وَأْمُرْ بِٱلْمَعْرُوفِ وَٱنْهَ عَنِ ٱلْمُنكَرِ وَٱصْبِرْ عَلَىٰ مَآ أَصَابَكَ ۖ إِنَّ ذَٰلِكَ مِنْ عَزْمِ

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ነቢያዊ ሱንና ውስጥ፦

ወደ ነቢያዊ ሐዲሶች ዐጸድ ከሄድን፣በምስጉን ስነምግባራትና በትሩፋት መርሆዎች የጎመሩ፣ልንቀጥፋቸው የምንችል ብዙ የኢማን ዛፎችን እናገኛለን። ከነዚህ ውስጥ፦

- ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ገር፣ለስላሳ፣የማያካብድና ለሰዎች ቅርብ የሆነ ሰው ሁሉ በእሳት ላይ እርም ተደርጓል።›› [በትርምዚ የተዘገበ]

- የአላህ መልክተኛ ﷺ ለአንድ ሶሓቢይ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹አላህ የሚወዳቸው ሁለት ባሕርያት አሉህ፦ ቻይነት (ታጋሽነት) እና ረጋ ባይነት።›› [በአሕመድ የተዘገበ]

- በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹እኔ ዘንድ ያለውን ነገር ከናንተ ቆጥቤ አላስቀምጥም፤ራሱን ቁጥብ ማድረግ የፈለገን ሰው አላህ ቁጥብ ያደርገዋል፤ራሱን ማብቃቃት የፈለገን ሰውም አላህ የተብቃቃ ያደርገዋል፤ራሱን ማጽናናት የፈለገን ሰውም አላህ ያጽናነዋል፤ለማንም ሰው ከትእግስት የበለጠ መልካምና ሰፊ ስጦታ አልተሰጠም።›› [በሙስሊም የተዘገበ]

- በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ሀብታምነት በንብረት ብዛት ሳይሆን፣ሀብታምነት የመንፈስ ሀብታምነት ነው።›› [በቡኻሪ የተዘገበ]

- የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ሰዎችን የማያመሰግን አላህን አያመሰግንም።›› [በአሕመድ የተዘገበ]

- በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ራሳችሁን አስተናንሱ (ትሁት ሁኑ)፤አንዳችሁ በሌላኛው ላይ ወሰን አይለፍ የሚል ከአላህ ተላልፎልኛል።›› [በእብን ማጃህ የተዘገበ]

- በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ሁሉም መልካም ሥራ ሶደቃ ነው፤ከመልካም ሥራ ውስጥ አንዱ፣ወንድምህን በፈካ ፊት መቀበል ነው፤ከራስህ ባልዲ ወደ ወንድምህ ዕቃ ውሃ መገልበጥም ነው።›› [በትርምዚ የተዘገበ]

በመጨረሻም በእውነተኛው ደስተኝነትና በመልካም ስነምግባራት መካከል ያለውን ግንኙነት፣በጣም ጥብቅ ጽኑና የተሳሰረ ጠንካራ ግንኙነት ሆኖ እናገኛለን። ግብረ ገብነትና መልካም ጠባይ ለሰው ልጆች ደስተኝነትና መታደል ብቸኛው ምንጭ ነው። ያለ ምስጉን ስነምግባር ደስተኝነት ፈጽሞ የሚታሰብ አይደለም። መልካም ስነምግባር በሌለበት ሁኔታ የሰው ልጅ በሕይወቱ ውስጥ ተስፋ መቁረጥን፣ጭንቀትን፣አበሳባና መከራን፣ውጥረትና መብሰልሰልን ብቻ ነው የሚያመርተውና የሚሰበስበው። በመሆኑም ደስተኝነትና መታደልን ፍለጋ፣የሰው ልጅ መልካም ስነምግባራትን እንዲላበስ ከሚገፋፉ አበይት ጉዳዮች ዋነኛው ነው። ምክንያቱም ያለ ምስጉን ስነምግባር ለአንዲት ሰከንድ እውነተኛውን ደስተኝነትንም ሆነ አንድም ቀን እርካታና መታደልን መጎናጸፍ እንደማይችል በእርግጠኝነት ያውቃልና።



https://www.path-2-happiness.com/am